# የገንዘብ ሚኒስቴር

## የካፒታል ሀብቶችን በማስተላለፍ በሚገኝ ጥቅም ላይ ስለሚከፈል ግብር አፈፃፀም የወጣን መመሪያ ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 267/2013

**ገንዘብ ሚኒስቴር**

**ነሐሴ 2012 ዓ.ም**

## የካፒታል ሀብቶችን በማስተላለፍ በሚገኝ ጥቅም ላይ ስለሚከፈል ግብር አፈጻጸም የወጣውን መመሪያ ቁጥር 201/2013 ለማሻሻል የወጣ መመሪያ 267/2013

1. **አውጪው ባለሥልጣን**

የገንዘብ ሚኒስቴር በፌደራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 99(2) እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410/2009 አንቀጽ 56(1) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

2. **ማሻሻያ**

የካፒታል ሀብቶችን በማስተላለፍ በሚገኝ ጥቅም ላይ ስለሚከፈል ግብር አፈጻጸም የወጣው መመሪያ ቁጥር 201/2013 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

1. የመመሪያው አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ (1) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ (1) ተተክቷል፡፡

   "1. "ግብር የሚከፈልበትን ሀብት በማስተላለፍ የተገኘ ጥቅም" ማለት ሀብትን በማስተላለፍ የተገኘው የገንዘብ ማጠን ሀብቱ በተላለፈበት ጊዜ ከነበረው ዋጋ በልጦ የተገኘው የገንዘብ ማጠን ሲሆን፣ መብትን ወይም ምርጫን በማስተላለፍ የሚገኝን ጥቅም ይጨምራል፡፡"

2. የመመሪያው አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (1) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (1) ተተክቷል፡፡

   "6(1). በአዋጁ አንቀጽ 21(4) በተደነገገው መሠረት አንድ የንግድ ሥራ ሀብት በአዋጁ አንቀጽ 59 መሠረት ግብር የሚከፈልበት ከሆነ፣ የንግድ ሥራ ሀብቱን በማስተላለፍ ከተገኘው ገቢ ወስጥ ከንግድ ሥራው ሀብት የተጣራ የማዝገብ ዋጋ የሚበልጠው ለንግድ ሥራው ሀብት የተደረገው ወጪ በንግድ ሥራው ገቢ ወስጥ የሚካተት ሲሆን፣ የንግድ ሥራው ሀብት በተላለፈበት ጊዜ ከነበረው ዋጋ በልጦ የተገኘው ማጠን በዚህ መመሪያ መሠረት ግብር ይከፈልበታል፡፡"

20. **መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ የገቢ ግብር አዋጁ ሥራ ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

*አዲስ አበባ ነሐሴ 07 ቀን 2012 ዓ.ም.*

*አህመድ ሺዴ*
*የገንዘብ ሚኒስትር*